# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 195 የካቲት 1 2004 ገጽ 1


አገራችንን ለመለስ ዜናዊና ዘራፊ ቡድኑ ለቀን እኛ በየሰው አገር ስንከራተት እስከመቼ እንዘልቃለን? መቼ ነው አገራችንን፣ ህይወታችንን፣ ተስፋችንን ከመለስ ዜናዊ መዳፍ ነጥቀን የራሳችን የምናደርገው? መቼ ነው በራሳችን ችሎታና ብቃት ላይ እምነት የሚኖረን? መቼ ነው "ኢትዮጵያ የኛ አገር ናት!!!" የምንለው?

ስደት ይብቃ!!! መሰደድ ግድ ከሆነም እዚያው አገራችን ውስጥ እንሰደድ!!! የኢትዮጵያዊያን ስደትና ፍልሰት እንዲያበቃ የምትፈልጉ ሁሉ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄን የሚያራምደውን ትግል ተቀላቀሉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ በዘጎች ላይ እያደረሰ ያለውን አፈናና እስር የአገሪቱን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ነው ሲል ገለጸ። በተለመደው ድንፋታና ዛቻ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ህብረት የሆነውን መድረክን በሽብርተኝነት መፈረጁን ገፍቶበታ

ከአንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ተመራጭ በቀር 544ቱን የፓርላማ መቀመጫ በጉልበቱ የተቆጣጠረው ዘረኛው መለስ ዜናዊ ባለፈው ረቡዕ ካድሬዎቹ ፊት ባቀረበው የስድስት ወር ሪፖርት፤ የፈጠራ ወንጀል ተመስርቶባቸው ወህኒ እየማቀቁ በሚገኙት ጋዜጠኞችና ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ላይ የተሰጠውን ፍርደ ገምድል ውሳኔ በማወደስ አሁንም ገና ያልተያዙ በርካታ ሰዎች መድረክ ውስጥ እንዳሉ በተለመደው ድንፋታና ዛቻ ገለጸ።

በአገሪቱ ውስጥ እየተባባሰ በመጣው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ምክንያት የራሱ አባላትና ደጋፊዎች ሳይቀሩ እየተንሸራተቱ መምጣታቸው ከፍተኛ ስጋትና ድንጋጤ የፈጠረበት መለስ ዜናዊ፤ የፓርላማ ውስጥ ድስኩሩን ጀምሮ ያጠናቀቀው ፊቱን አኮማትሮና ተቆጥቶ እንደሆነ በቴለቪዥን የተመለከቱ ሁሉ ታዝበዋል።

በራሱ ካድሬዎች በተሞላው ፓርላማ ውስጥ አስቀድሞ የተሰጣቸውን ጥያቄ ተራ በተራ ያቀረቡት ሰዎች በጸረሽብርተኝነት አዋጁ መሠረት ታሰሩ የተባሉ የአገር ውስጥና የአገር ውጪ ጋዜጠኞች እንዲሁም ተቃዋሚ ፖለቲከኞ ጉዳይ ለምን አለም አቀፉ ውግዘት እንዳስከተለ ላቀረቡለት ጥያቄ፤ "የሲውድን ጋዜጠኞችን በማሰራችን እንደ ስድ ተቆጥሮብናል ዘመቻም የተከፈተብን ከዚያ አንጻር ነው። ስለዚህ ሉአላዊነታችንን ማስከበር ካለብን የሚያካሂዱብንን ዘመቻ መቋቋም አለብን የሚል" ከዋናው ምክንያት ጋር ምንም ግንኙነት የሌው ምላሽ ሰጥቶአል።

መለስ ዜናዊ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ በሥልጣን የሚቀናቀኑትንና እርሱ የሚፈጽማቸውን ግድያዎችና ሰቆቃዎችን የሚያወግዙ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችንና የምዕራባዊያን ለጋሽ አገሮችን በሙሉ ሉአላዊነት በመድፈር ወንጀል ይከሳቸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋው ሙስናና ኢፍትሃዊነት በአስቸኳይ መፍትሄ ካልተገኘለት የቱንዚያን አይነት አብዮት እንደሚያስከትል አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ አስጠነቀቀ

አፍቃሬ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ባለፈው ዕሁድ ጥር 27፣ 2004 ዓ/ም ህትመቱ "ፈንጂ አምካኝ በአስቸኳይ!! ሙስና በኢትዮጵያ አገር አጥፊ የተቀበረ ፈንጂ ሆኗል" በሚል ርዕሰ አንቀጽ ይፋ እንዳደረገው በአገሪቱ ውስጥ የሰፈነው ሙስና ህገ መንግሥታዊ፤ ህጋዊና ፍትሃዊ ይሆናሉ ተብለው የተደነገጉትንና የታቀዱትን ተግባራት በሙሉ በማደብዘዝ ድራሻቸውን አጥፍቶ የበላይነቱን ይዞአል።

ከሙስናው መስፋፋት በተጨማሪ "ዴሞክራሲ፣ ሰብዓዊ መብትና ፍትሕ እየተቀረቀሩ፣ እየተደነቀሩ፣ እየተንገዳገዱና እየተሰባበሩ ‹‹ምን እየሆኑ ነው;›› የሚያስብል የህልውና ጥያቄ እያስነሱ ናቸው" ያለው ሪፖርተር፤ ይህ ተግባር ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደ ሰደድ እሳት እየተዛመተና ሥር እየሰደደ ሕዝብን እያማረረ ከመሄዱም በላይ፣ ተባብሶና ተጠናክሮ በማንኛውም ጊዜ አገርን የሚያወድም የተቀበረ ፈንጂ ሆኗል ብሎአል፡፡

የቀድሞ የህወሃት ታጋይና በአንድ ወቅት የወያኔ ፕሮፖጋንዳ ዳይሬክተር ሆኖ ሲያገለግል የነበረው የአቶ አማረ አረጋዊ ንብረት የሆነው ሪፖርተር በዚህ ህትመቱ ይፋ እንዳደረገው፤ ወያኔ እመራበታለሁ በሚለው ሕገ መንግሥት "ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ነው" የተባለ ቢሆንም አሁን በመላው አገሪቱ በተንሰራፋው ሙስና ምክንያት ግን "ገንዘብና ጥቅማ ጥቅም የሚሰጥ የበለጠ እኩል ነው፡፡ ጉቦ የማይሰጡና ጥቅማ ጥቅም የማያቀርቡ ዜጎች ግን ተጎጂ እየሆኑ ነው" ብሎአል፡፡

"የዕቃ ግዥ ጨረታዎች፣ ኢንቨስትመንቶች፣ ፈቃዶች፣ ብድሮች፣ ወዘተ በሙስና እየተመሰቃቀሉ ይገኛሉ" ያለው ሪፖርተር "ትላልቅ ጨረታዎችና ግዥዎች በተለይም በውጭ ምንዛሪ የሚፈጸሙ ጨረታዎችና ግዥዎች ከግል ጥቅም ጋር እየተያያዙ አገርን ለአደጋ እየዳረጉ ያሉ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ት/ቤቶች ከማስተማሪያነት ይልቅ በካድሬ መመልመያነት ወያኔን እያገለገሉ መሆናቸው ታወቀ

በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛዎች (TVET) 10+1፣ 10+2 እና 10+3 ደረጃዎች ላይ የሚመማሩ ታዳጊ ወጣቶች ገና ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ የወያኔ ድርጅቶች አባላት እንዲሆኑ ተጽዕኖ እንደሚደረግባቸው የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው የማሠልጠኛው ተማሪዎችና ወላጆቻቸው አረጋገጡ።

እንደወላጆችና ተማሪዎች መረጃ፤ የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ካድሬዎች በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች ውስጥ ተማሪ የሆኑትን "አምስት አምስት ሆናችሁ ተደራጁና ወይ ሥራ ይሰጣችኋል አሊያም የራሳችሁን ሥራ ትጀምራላችሁ" በማለት እንደሚደልሉዋቸውና "ሲደራጁ በሙያ ፋንታ የፓለቲካ ትምህርት እንደሚሰጣቸው እንዲሁም የሰፈራቸውን ሰውና ቤተሰቦቻቸውን ሳይቀር እንዲሰልሉ እንደሚነገራቸው በምሬት ይናገራሉ።

የወደፊት የሥራ ዕድላቸውና የመማር ነጻነታቸው አሳስቦአቸው ያለውደታቸው ለመደራጀት የተገደዱት እነዚህ ተማሪዎች አምስት አምስት ሆነው ከተደራጁ በኋላ እያንዳንዱ ኮሚቴ ግኑኝነቱ ከቀበሌዎች ጋር እንደሆነና መደራጀትን እንቢኝ ያሉ ደግሞ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ የትምህርት ማስረጃቸው እንደማይሰጣቸው ለማወቅ ተችሎአል።

ከፍላጎታችን ውጪ ተገደን የኢህአደግ አባል ሆነን ተደራጅተናል በማለት እያማረሩ ያሉ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው ወጣቶች "ከመጀመሪያው ተደራጁ ስትባሉ ለምን አንፈልግም አትሉም? ነበር" ተብለው ሲጠየቁ "አልደራጅም ማለት አይቻልም። የየትኛው ድርጅት አባል ነህ ይባልና ክትትል ይደረግብሃል? ገብቼ ልውጣ ማለትም አይቻልም። እንደማፍያ ድርጅት ከተገባበት አይወጣም። የምናደርገውን አጥተን ተቸግረናል" ሲሉ መልሰዋል። ወጣቶቹ በራሳቸው ገንዘብ የራሳቸውን ሥራ ለመጀመር እንኳን እንደማይችሉ "ገንዘቡን ከየት አመጣህ፤ የትኛው ድርጅት ሰጠህ?" ተብለው እንደሚጠየቁና የተለያየ ግልጽና ሥውር ማስፈራራት እንደሚደርስባቸው ይናገራሉ። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የኤድስ ፈንድ ለፖለቲካ ድጋፍ መሸመቻ እየዋለ መሆኑ ተነገረ

ተስፋ ጎህን ለረጅም አመታት በፕሬዚዳንትነት የመሩት አቶ ታደሰ አይናለም፣ በኤች አይቪ ቫይረስ ለተጠቁ ወገኖች ተብሎ ከግሎባል ፈንድ፣ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና ከተለያዩ በርካታ አለማቀፍ ድርጅቶች የሚለገሰው በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ፣ በመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ትእዛዝ ብቻ ከታለመለት አላማ ውጭ እንደሚውል ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) መግለጻቸውን ኢሳት ዘገበ።

አቶ ታደሰ ለኢሳት እንደተናገሩት የወያኔ ፕሮፖጋንዳ መሳሪያ ሆነው ህዝባችንን በማደናገርና በማደንዘዝ ለተሰማሩት ለሬዲዮ ፋናና ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በማስታወቂያ ስም በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለኤድስ ተብሎ በዕርዳታ ከተለገሰ ገንዘብ ውስጥ እንዲፈስ ይደረጋል። ሬዲዮ ፋና በአዲስ አበባ ውስጥ የገነባው ዘመናዊ ህንጻ ገንዘብ አብዛኛው ምንጭ የኤድስ ፈንድ መሆኑ ይታወቃል።

የመለስ ዜናዊ ዘራፊ አገዛዝ በተለያዩ መንገዶች ለእርዳታ ተብሎ የሚሰጠውን ገንዘብ ለፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ እንደሚያውለው ሂውማን ራይትስ ወች መግለጡ አይዘነጋም።

## በአዲሱ የዘረፋ የሊዝ አዋጅ ላይ የሚቀርበው ተቃውሞ እንደቀጠለ ነው

ወያኔ የዘረፋ አድማሱን ለማስፋት ሲል የሚያወጣቸው አዋጆችና ደንቦች ህዝቡን እያስመረሩት ነው። አዲሱን የመኖሪያ ቤቶችን ጣራና ግድግዳ ብቻ የሚያስቀር አዋጅን ማስፈፀም ለራሱ ለወያኔም ችግር ሆኖበታል ተብሎአል። በሊዝ አዋጁ ምክንያት ባንኮች ለብድር ዋስትና የያዟቸውን ቤቶች በሚመለከት ማድረግ የሚገባቸውን ማወቅ ተስኗቸው እየተቸገሩ እንደሆነ ለባንኮች ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ከላኩት መረጃ ለማወቅ ተችሎአል።

ወያኔ የህዝብን ንብረት በመቀማት ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ንብረት አልባ ለማድረግ ሲል ያወጣው ይህ የሊዝ አዋጅ ባንኮች ላበደሩዋቸው ብድሮች በያዙዋቸው መያዣዎች ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ በማጥናት ላይ መሆናቸውን ሪፓርተር ጋዜጣ ዘገቦአል። ከዚህ በፊት የቤት ዋጋ ሲገመት መሬቱ እስከ 40 በመቶ ይያዝ እንደነበር ይኸው ጋዜጣ ገልጿል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት የግንቦት 7 ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ "የሸፍቶች ካፒታሊዝም" በሚል አርዕስት የባንክ ብድር እንዴት ለዘረፋ እንደሚውል ማብራራታቸው ይታወሳል። አዲሱ የሊዝ አዋጅም "የሸፍቶች ካፒታሊዝም" ቀጣይ እርምጃ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ።

## አገራችን ውስጥ እንሰደድ!!!

ስደት፣ በኢትዮጵያ የረዠም ጊዜ ታሪክ ያለው ክስተት ነው። ሆኖም በታሪካችን ውስጥ የምናውቀው የአገር ውስጥ ስደትንና ፍልሰትን ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ የእርሻ፣ የመኖሪያና የመንደር መሥሪያ መሬት ፍለጋ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር፤ ሲገብርና ሲያስገብር የኖረ ህዝብ ነው። አሁን ያለው የማኅበረሰባችን ስብጥር የዚህ የምዕተ ዓመታት የአገር ውስጥ ስደትና ፍልሰት ውጤት ነው። በአገራችን ውስጥ ሲደረጉ የነበሩት የህዝብ ፍልሰቶች በሙሉ ሰላማዊ አልነበሩም። አንዳንዶቹ ፍልሰቶች በመረሩ ግጭቶች የታጀቡ፤ ሰዎች ለመከራ የተዳረጉባቸው ነበሩ። ሆኖም ግን ፍልሰቱ፣ ስደቱ፣ መገበርና ማስገበሩ በራስ አገር ውስጥ የተከናወኑ መሆናቸው አንድ ትልቅ ቁምነገር ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ ግጭቶችም ቢኖሩ በይገባኛል፣ አይገባህም ሙግት፤ ለመብትና ለክብር የተደረጉ ተጋድሎዎች የነበሩ መሆናቸው ሌላው አቢይ ጉዳይ ነው። ያኔ ግጭቶች እንኳን ቢኖሩ በሁለት ለራሳቸው ክብር በሚሰጡ ቡድኖች መካከል የተደረጉ ፍልሚያዎች ነበሩ።

በአለፉት ሃምሳ ዓመታት፣ በተለይም ደግሞ በቅርቦቹ ሁለት አስርት ዓመታት፣ ውስጥ እያየነው ያለው ስደትና ፍልሰት ግን በዓይነቱ ፈጽሞ የተለየ ነው። ተሰዳጁ እግሩ ባደረሰው የሚያገኘውን ሰው ሁሉ አዘኔታን እንዲቸረው የሚለምን እንጂ የሚያስከብረው አንዳችም መብት የሌለው ምስኪን ሆኗል። በተለይ አሁን፣ በመለስ ዜናዊ የአገዛዝና የአፈና ዘመን፣ ያለው የስደትና ፍልሰት ዓይነት በአስነዋሪነቱ ወደር የለውም።

ከጥቂት አስርት ዓመታት በፊት ርቆ ተጓዡ ባብዛኛው የተማረውና ከተማ ቀመሱ ወጣት ነበር። ዛሬ ግን አርሶ አደሮች ጎጆዓቸውንና ልጆቻቸውን ጥለው በረሃዎችንና ደኖችን አቋርጠው ደቡብ አፍሪቃ ድረስ በእግር ለመጓዝ ሲነሱ ማስተዋል ልብን ይሰብራል። ወጣት እናቶች ልጆቻቸውን ጥለው ተበድረውና ተለቅተው ወደ አረብ አገራት ለግርድና ሲፈልሱ ማየት እጅግ ያሳዝናል።

ዛሬ የምንሰደደው እንደ ድሮው መሬት ፍለጋ አይደለም። ዛሬ እየተሰደድን ያለነው ሌላ መሬት የመያዝ ፍላጎትም ሆነ ተስፋ ሳይኖረን የራሳችንን ለም መሬት ለቀን ነው። ዛሬ የምንሰደደው በሌላ ቦታ የራሳችንን መንደር ለመመሥረት አይደለም። እየተሰደድን ያለነው የድሃ መንደራችንን ለጉልበተኛ ሃብታሞች አስረክበን፤ ራሳችንን መድረሻ የለሽ፣ አገር የለሽ፣ መንደር የለሽ አድርገን ነው።

ኢትዮጵያዊያን የገባንበት የተስፋ ማጣት ቀውስ ጥልቀት መገንዘብ ያዳግታል። የኢትዮጵያዊያን ዘግናኝ ስደት ታሪኮች ቢፃፉ ብዙ ድርሳናት ይወጡታል። አገሮችን በእግር ለማቋረጥ ተነስተው፤ መንገድ ጀምረው በድካም፣ ረሃብና ጥም የተፈቱ፤ በጉልበተኞች የተዘረፉ፣ የተደፈሩ፣ የተገደሉ ቤቱ ይቁጠራቸው። በሱዳንና ሊቢያ አድርገው፤ ሰሃራ በረሃን አቆራርጠው በትናንሽ ጀልባዎች ተሳፍረው አውሮፓ ለመግባት ሲሞክሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን መነገር የማይችል መከራ ደርሶባቸዋል። ቀይ ባህርን በታንኳዎች ተሻግረው የመን ለመግባት ሲሞክሩ ሰጥመው የቀሩ ብዙዎች ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥቃቅን "አገልግሎት" ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች የሚከፍሉት ገንዘብ መጠን ይገርማል። የኢትዮጵያዊያን የስደት "ገድል" ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። አንድ ሰው ከኢትዮጵያ ተነስቶ ምዕራብ አፍሪቃ ደርሶ፤ አትላንቲክ ውቅያኖስን ተሻግሮ፤ ደቡብ አሜሪካ ገብቶ፤ ከዚያ ተሽሎክሉኮ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለመግባት ስንት ጊዜ ከሞት ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ አለበት? የኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ህይወት በየእለቱና ደቂቃው ከሞት ጋር ድብብቆሽ መጫወት ነው። በኢትዮጵያ ያሉ እስር ቤቶች ብቻ ሳይሆን የሌሎች አገራት እስር ቤቶችም በኢትዮጵያዊያን እየተሞሉ ነው። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ያሉበት ሁኔታ እጅግ አሳዛኝ ነው።

እነዚህን ዘግናኝ ታሪኮችን እየሰማንም ቢሆን ዛሬም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ስደት የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁዎች ናቸው። በትምህርት የገፉውም፣ ያልገፉውም፤ ከተሜውም፣ ባላገሩም፣ ወንዱም፣ ሴቱም ስደት ላይ ነው። የኢትዮጵያ ልጆች መንገድ ላይ ናቸው። ኢትዮጵያዊያን በሁሉም አቅጣጫዎች እየተበተንን ነው።

### ምን ተሻለን?

በስደት ሞትን ፊትለፊት ለመግጠም የሚደፍረው ወጣት ለስደቱ ምክንያት የሆነውን ኢፍትሃዊ አገዛዝን የመቀየር ድፍረት እንዴት ሊያጣ ቻለ? ለምንድነው ህዝባችን በራሱ እና በአገራችን ላይ ፈጽሞ ተስፋ የቆረጠው? በመሰደዳችን፣ በመፍለሳችን፣ በመሸሻችን የሚጠቀመው ማነው? ለምንድነው ስደታችንን አገራችን ውስጥ የማናደርገው?

በኢትዮጵያዊያን መከራና ስቃይ ወያኔ ይስቃል። ወያኔ ማረስ ባይችል ለም መሬታችንን ለህንድና ለቻይና ሃብታሞች መሸጥ አያቅተውም። እያደረገ ያለውም ይህንኑ ነው። የኢትዮጵያዊያን ከኢትዮጵያ መሰደድ ለወያኔ ፌሽታና ፈንጠዚያ ነው።

ኢትዮጵያዊያን በበረሃ ንዳድ ተቃጥለው ቢያልቁ፤ የሰውነታቸው አካሎች እንደመኪና መለዋወጫ ቢሸጡ፤ ባህር ውስጥ ቢሰጥሙ፤ እህቶችና እናቶች ቢደፈሩ፣ ቢታሰሩ፣ ቢጉላሉ ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ደስታ ነው። የኢትዮጵያዊያን መሸሽ የመለስን አልጋ ያፀናል። "አገሬ ነው!!!" የሚል ትውልድ እስኪመጣ መለስ ተዝናንቶ ይገዛል።

የስደት ጉዞ መከራዎችን አልፈው አንዳንዶች ተሳክቶላቸው አሰቡበት አገር ከደረሱ መለስ ዜናዊ "በዲያስፖራ ፓሊሲው" ይቀበላቸዋል። እንደምንም ብለው ለዘመዶቻቸው ገንዘብ እንዲልኩ በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ችግሩን ይወጣባቸዋል። ከስደተኞቹ መካከል ተፍጨርጭረው በእግራቸው የቆሙ ከተገኙ ደግሞ "ልማታዊ ኢንቨስተር" እንዲሆኑ በመጋበዝ የብዝበዛ ወፍጮው አካል ያደርጋቸዋል።

ስንቴ እንሞኝ?

አገራችንን ለመለስ ዜናዊና ዘራፊ ቡድኑ ለቀን እኛ በየሰው አገር ስንከራተት እስከመቼ እንዘልቃለን? መቼ ነው አገራችንን፣ ህይወታችንን፣ ተስፋችንን ከመለስ ዜናዊ መዳፍ ነጥቀን የራሳችን የምናደርገው? መቼ ነው በራሳችን ችሎታና ብቃት ላይ እምነት የሚኖረን? መቼ ነው "ኢትዮጵያ የኛ አገር ናት!!!" የምንለው?

ስደት ይብቃ!!! መሰደድ ግድ ከሆነም እዚያው አገራችን ውስጥ እንሰደድ!!! የኢትዮጵያዊያን ስደትና ፍልሰት እንዲያበቃ የምትፈልጉ ሁሉ ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄን የሚያራምደውን ትግል ተቀላቀሉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ በዘጎች ላይ እያደረሰ ያለውን አፈናና እስር የአገሪቱን ሉአላዊነት … (ከገፅ 1 የዞረ)

በሥልጣን ላይ ከወጣ 21ኛ አመቱን እያገባደደ ያለው መለስ ዜናዊ ሆን ብሎ በፈጠረው ሙስና፤ዝርፊያና የስልጣን ብልግና የተፈጠረውን ቀውስ በሌሎች ላይ በማላከክ ለራሱ መውጫ ያበጀ እየመሰለው ለርሱና ለፓርቲው ባላቸው ታማኝነት በየቦታው የጎለታቸውን ሹማምንቶቹን የመንግሥት ሌቦች እያለ ሲያብጠለጥል በተስተዋለበት ባለፈው ረቡዕ የፓርላማ ስብሰባ፤ በመድረክ ውስጥ አሁንም ቁጥጥር ሥር ያልዋሉ ሽብርተኞች አሉ በማለት ለማስፈራራት ሲፍጨረጨር ታይቶአል።

መለስ ዜናዊና ባሌቤቱ አዘብ መስፍን ባለፉት 20 አመታት ውስጥ የናጠጡ ሃብታም ለመሆን ከበቁት የቀድሞ የህወሃት ታጋዮች ተወዳዳሪ የሌላቸው ዲታዎች መሆናቸው እየታወቀ በየስብሰባ መድረክ የበታቾቹን ሌቦች እያለ መሳደቡ መቀጠሉ ብዙዎችን የኢህአግ አባላትን እያስቆጣ ነው ተብሎአል።

## በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋው ሙስናና ኢፍትሃዊነት በአስቸኳይ መፍትሄ ካልተገኘለት የቱንዚያን … (ከገፅ 1 የዞረ)

መሆኑን ገልጾ፤ "መንግሥት ሁለት መቶ ቢሊዮን ብር ዕዳ አለበት ሲባል ገንዘቡ እንዳለ ለልማት እየዋለ ነው ማለት አንዳልሆነ" በመግለጽ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅና ባለንበረት የሆነው አማርረ አረጋዊ የቀድሞ ጓዶቹ የሚፈጽሙትንና በቅርበት የሚያውቃቸውን ሃቆች በጋዜጣው ርዕሰ አንቀጽ አስፍሮአል።

በሪፖርተር ዋና አዘጋጅ እምነት ይህንን የመሰለ ሙስናና ኢፍትሃዊነት እየፈጠሩ ያሉት ከላይ ከሚንስትርነት ማዕረግ ጀምሮ እስከ ታች ዘበኛው ድረስ በተዋረድ ያሉ የመንግሥት ሠራተኞች ናቸው። ይህም በመሆኑ ተደጋግሞ የሚገለጸውና የጋዜጣው አዘጋጅ ጨምሮ አብዛኞቹ ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው የሚስማሙባቸው መሻሻል የተመዘገበባቸው የመሰረተ ልማት ዘርፎች የህዝቡን ተቃውሞና ብሶት ሊያስታግሱ እንደማይችሉ በዚህም ምክንያት ታምቆ ያለና ሊፈነዳ ጊዜውን እየተጠባበቀ ያለ አደጋ በመኖሩ አስቸኳይ መፍትሄ ካልተፈለገለት ተቃዋሚዎች ደጋግመው እንደሚናገሩት በቱኒዚያና በተቀሩት አረብ አገሮች የታየው አይነት ህዝባዊ ቁጣ መፈንዳቱ አይቀሬ ሆኖአል።

የሪፖርተር ጋዜጣ ዋና ባለቤት አማረ አረጋዊ የቀድሞ ህወሃት ታጋይ የነበረና የራሱን የህትመት ሥራ ለመጀመር ከሥልጣን እስከተሰናበተ ድረስ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ መምሪያ ዳይሬክተር በመሆን የወያኔ አገዛዝ በሥልጣን ላይ እንዲደላደል የበኩሉን አስተዋጽኦ ከማበርከቱም ሌላ የቀድሞ አለቆቹ የተዘፈቁበትን ሙስናና የሃብት ዘረፋ አልፎ አልፎ በመጠቆም አገዛዙ የህዝብ ተቃውሞ ከሚያባብሱ ተግብሮቹ እንዲታቀብ ምክር አዘል መረጃዎችን በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

ሆኖም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ተራድኦ እና ታዋቂ የሆኑ አለም ቀፍ የፋይናንስ ተቋሞች ባለፉት 9 አመታት ውስጥ ብቻ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት በህገ ወጥ መንገድ 11 ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከአገር ማሸሻቸውን ይፋ ማድረጋቸውን አስመልክቶ ሪፖርተር ያለው ነገር ግን የለም። በተመሳሳይም ሪፖርተር ጋዜጣ ስለ መለስ ዜናዊና የሙስና እመቤት የሚል ቅጽል ሥም ለተሰጣት ባለቤቱ አዜብ መስፍን ስለተዘፈቁበት ሙስናና ሃብት ዘረፋ አስመልክቶ ምንም ቃል ባለመናገሩ የተቆጡ የህዝብ አስተያየቶች በጋዜጣው ድረ ገጽ ላይ እየወጡ ናቸው።

## ሰቆቃን ለማስቆም በጋራ እንነሳ!!!

### ግንቦት 7 በርዕሰ አንቀጽ ቁጥር 134 ለህዝብ አቅርባው የነበረ ጥሪ

ከወያኔ እስር ቤቶች የሚደርሱን መረጃዎች ህሊናን የሚረብሹ ናቸው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላት በእስር ላይ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ የሚፈጽሙት ሰቆቃ (ቶርቸር) በአስከፊ ሁኔታ ጨምሯል።

በጭካኔው "ተወዳዳሪ የለውም" ሲባል በነበረው የደርግ ዘመን እንኳን የማይታወቁ የሰቆቃ ዓይነቶች ዛሬ በንፁሃን ዜጎች ላይ እየተፈጸሙ ነው። ለማስረጃ ያህል:-

- ወንዶች የዘር ፍሬዎቻቸውን በመዶሻ ይቀጠቀጣሉ፣
- ሴቶች ጡቶቻቸውን ይረገጣሉ፤ ክብረ-ነክ ተግባራትም ይፈጸምባቸዋል፣
- በኤሌክትሪክ በሚሰራ ማሞቂያ የእስረኞችን ጭንቅላት በማጋል እንዲሰቃዩ ይደረጋል፣
- ከወንበር ጋር አቆራኝቶ ለሳምንት ያህል ማሰር በጣም እየተዘወተረ ያለ የሰቆቃ ዓይነት ሆኗል፣
- በጠባብ ክፍል ውስጥ ለብቻ ዘግቶ ለወራት ማቆየት የተለመደ ነገር ነው፣
- ከቆዳ በተሰራ ጅራፍ መግረፍ ድሮም ያለ ቢሆንም አሁን ተጠናክሮ ቀጥሏል፤ በደርግ ጊዜ የነበሩ ገራፊዎች ከያሉበት እየተፈለጉ እንደገና ለገረፋ ተቀጥረዋል፣
- በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ካራቴና ጁዶ መለማመድ፤ በስለት መቆራረጥ ወጣት የወያኔ "ተተኪዎች" የሚወዱት መዝናኛ ሆኗል፣

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ አሰቃቂ የሰቆቃ ዓይነቶች የወያኔ እስር ቤቶች መለያ ባህሪያት ናቸው።

የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ ሰላዮች ሰቆቃን የሚፈጽሙ ስለመሆኑ በገሃድ አምነው አያውቁም። ሆኖም ግን ሰቆቃን የሚፈጽሙት ተከልለውና ተደብቀው አይደለም። ስንቱ ነው ከተማ ውስጥ በሰው መሃል የተደበደበው? ስንቱ ነው በአደባባይ የተረገጠውና የተዋረደው? በጠራራ ፀሃይ፤ ከተማ ውስጥ፤ ህዝብ መሃል ይህንን የመሰለ ሰቆቃ የፈጸመን እስር ቤት ውስጥ ከዚህ አንድ ሺህ ጊዜ የከፋ ነገር ከመፈጸም ምን ያግደዋል?

በማናቸውም ምክንያት ሰቆቃ መፈጸም እጅግ የተወገዘ እና ምህረት የማያሰጥ ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። የደህንነት ስጋትም ሆነ አደጋ ለሰቆቃ በምክንያትነት ሊቀርብ አይችልም። ሰቆቃን ተቀባይነት ያለው የምርመራ ዘዴ የሚያደርግ የወንጀል ዓይነት የለም። "ወንጀል መከላከል" ለሰቆቃ ተቀባይነት የሌለው ምክንያታቸው ቢሆንም እንኳን ወያኔዎች እሱንም በምክንያትነት ማቅረብ አይችሉም። የወያኔ ሰላዮችና ፓሊሶች ሰቆቃን የሚፈጽሙት የሚመረምሩት ብርቱ ወንጀል ስላለ አይደለም። ወያኔዎች በወያኔ ዳኞች ጉዳያቸው ያለቀላቸውና ወያኔያዊ ፍርደገምድል ፍርድ የተሰጣቸው ፍርደኞችንም ጭምር ያሰቃያሉ። ለወያኔ የሰቆቃ እውነተኛ ምክንያቶች ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያዉና እና ዋነኛው ምክንያታቸው የዘር ጥላቻ ነው። የወያኔ አረመኔዎች የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች የሆኑ ግለሰቦችን በደበደቡና ባዋረዱ መጠን አማራንና ኦሮሞን ያዋረዱ ይመስላቸዋል። ለዘመናት በልባቸው ውስጥ የተጠራቀመውን ጥላቻ በግለሰቦች ላይ ይወጡታል። እነዚህ በክፋት የተሞሉ ሰዎች ሲገርፉና ሲደበድቡ የሚሳደቡት፣ የሚራገሙት የተደብዳቢውን ዘር እንጂ ተደብዳቢውን በግል አለመሆኑ የደረሰበት ሁሉ ያውቀዋል።

ሁለተኛው ምክንያት የጉጅሌው አባላትና ተባባሪዎች ሰውን በማሰቃየት የሚደሰቱ እኩያን መሆናቸው ነው። ይህ የስነልቡና ህመም ምንጩ በራስ የመተማመን እጦት ነው። መንፈሰ ደካማ ሰው ውስጡ እየነገረው ያለውን ደካማነት በእጆቹ በሚሰነዝረው ዱላ ማስተባበል ይፈልጋል። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ እና ተባባሪዎቹ የሚያደርጉት ይህንኑ ነው። እጃቸው ውስጥ የገቡትን ወገኖቻችንን በማሰቃየት ትንሽነታቸውን ማሸነፍ ይፈልጋሉ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወገኖቻችን ላይ ዘግናኝ ሰቆቃዎችን በማድረስ ላይ ለምትገኙ የትግራይ ገዥ ጉጅሌ አባላት፣ ለቅጥረኞቻቸውና ተባባሪዎቻቸው በሙሉ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። ሰቆቃ ፈጽሞ ማምለጥ እንደማይቻል በደርግ ጊዜ የሰቆቃ ቀንደኛ መሪ ከነበረውና በአሜሪካ አገር ተከሶ ዛሬ በናንተው እስር ቤት ከሚገኘው ቀልቤሳ ነጌዎ ትምህርት ውሰዱ። የእናንተም መጨረሻ ከእነሱ የባሰ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን ተገንዘቡ።

ግንቦት 7 በሰቆቃ ላይ መረጃ ማሰባሰብ የጀመረ በመሆኑ ያላችሁን መረጃዎች

<u>በኢሜል</u> pr@ginbot7.org እና
<u>በፖስታ</u> P.O.Box: 56281, London N4 9BH, United Kingdom
8647 Richmond Highway, 652, Alexandria, VA 22309, USA

እንትልኩ ያሳስባል።

በመጨረሻም ሰቆቃን ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት የሚቻለው ወያኔን ማስወገድና በምትኩ ለሰው ልጅ ክብር ያለው በህዝብ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ በመሆኑ ለዚህ ግብ ሁላችንም በአንድነት እንነሳ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በሽብርተኝነት የፈጠራ ክስ ረጅም እስር ከተፈረደባቸው አንዱ የሆኑትን አቶ ዘሪሁን ገብረ እግዜሃብሔርን በሌሎች ላይ በሃሰት መስክረው በነጻ እንዲለቀቁ የቀረበላቸውን ጥያቄ ውድቅ በማድረጋቸዉ ለ17 አመት ጽኑ እስራት እንደተዳረጉ ታወቀ

በወያኔ የፈጠራ ክስ በሽብርተኝነት ተወንጅለው የ17 አመት ጽኑ ዕስራት የተፈረደባቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ ፕሬዚዳንት አቶ ዘሪሁን ገብረ-እግዚአብሔር ታስረው በወያኔ ምርማራ ክፍል በነበሩበት ወቅት በሌሎች ንጹሃን ላይ በሃሰት ከመሰከሩ በነጻ ሊለቀቁ እንደሚችሉ ቃል ተገብቶላቸው እንደነበረና እምቢኝ በማለታቸው አሁን ለተጣለባቸዉ የጽኑ ዕስራት ፍርድ ተዳርገዋል ሲል የአንድነት ልሳን የሆነው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዘገበ።

የወያኔ ፍርድ ቤት በተከሳሾቹ ላይ ፍርድ ከመስጠቱ አስቀድሞ ከእራሳቸው ከአቶ ዘሪሁን በጽሁፍ የተላከ ደብዳቤ በእጁ ላይ ገብቶ እንደነበረ የገለጸው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ፤ እጃቸው ተይዞ በቁጥጥር ሥር ከገቡበት ቀን ጀምሮ የወያኔ ወንጀል ምርመራ ሹሞች እሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በማግባባት በነ ኤልያስ ክፍሌ መዝገብ በተከሰሱት ላይ የሃሰት ምስክር አድርጎ ለማቅረብና በውለታው እርሳቸውን በነጻ ለመልቀቅ አድርጎት የነበረውን ጥረት ዝርዝር አቅርቦአል።

አቶ ዘሪሁን ወደ ወህኒ ከመውረዳቸው በፊት ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ በላኩት ደብዳቤ የወያኔ ወንጀል መርማሪዎች ልክ በታሰሩ ማግሥት ምርመራ ቢሯቸው ጠርተዋቸው "መቼም አንተ የአራዳ ልጅ ነህና እንደ ገጠር ልጅ ስለማትገግም እኛ በምንነግርህ መሠረት በመድረክ መሪዎች፣ በአንድነት ፓርቲ አመራሮችና በኤልያስ ክፍሌ ላይ ከመሰከርክ በነጻ ትለቀቃለህ " መባላቸውን ጠቅሰው "...ምንድነው የምመሰክረው ብዬ ስጠይቃቸው ሽብርተኞች ናቸው፤ ወንጀለኞች ናቸው፤ ይህን ይህን.. አድርገዋል ፤ እኔንም እንዲህ እንዲህ.. አድርግ ብለውኛል ብለህ ትመሰክራለህ" መባላቸውን አጋልጠዋል።

በሃሰት ላቀነባበሩት የፈጠራ ወንጀል የውሸት ምስክር ለማግኘት እየተሯሯጡ ለነበሩት የወያኔ ወንጀል ምርመራ ሹሞች የሚያስደነግጥ ምላሽ የሰጡት አቶ ዘሪሁን ገብረ-እግዚአብሄር ግን በእርግጥ መርካቶ ተወልደው መርካቶ ያደጉ የአራዳ ልጅ መሆናቸውን አምነው "የመርካቶ ልጅ አብሮ መብላት፤ አብሮ መሥራት፤ ለጓደኛውና ለእውነት ግንባሩን መስጠት እንጂ በማያውቀው ነገር የሐሰት ምስክር ሆኖ መቅረብን እንዳልሆነ በዚህም ምክንያት የአራዳ ልጅ በእምነቱ ይሞታል እንጂ ግብዝ አይሆንም፤ "እየሰማሁ ያደኩትም ለእውነት መቆምና በሐሰት አለመመስከርን ነው፤ ማስረጃ አለን ብላችሁ ከያዛችሁኝ በኋላ እንዴት እንዲህ ትሉኛላችሁ?"ማለታቸውን ጋዜጣው ዘግቦአል።

አቶ ዘሪሁን ለፍኖት በላኩት ደብዳቤ "በሰጠኋቸው ምላሽ የተበሳጩት መርማሪዎች ፍ/ቤቱን የምናዘው እኛ ነን፤ እንቢ ካልክ የ20 ዓመት እስር ይጠብቅሀል፤ የሚደርስብህን ሁሉ ታያለህ" ብለው እንዳስፈራሩዋቸውና እርሳቸው ግን " የፈለጋችሁትን አምጡ እንጂ በሐሰት ምስክር ሆኜ አልቀርብም "እንዳሉ ጠቅሰዋል።

በደረሰባቸው ዛቻና ማስፈራሪያ አለመበገራቸውን የተመለከቱት የወያኔ መርማሪዎች ዜደያቸውን በመቀየር ፊታቸውን ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዳዞሩና ቤተሰቦቻቸውን ምርመራ ቢሮ ድረስ ጠርተው "ይህንን ሰው ምከሩት፤ ለሰው ብሎ ራሱንና ቤተሰቡን እየጐዳ ነው፤ እሱ እንዴት የቤተሰብ ኃላፊነት አይሰማውም? እኛ እሱን ለመርዳት ከፍተኛ ጥረት እያደረግን እሱ ግን እንቢ እያለ ነው፤ ቀላሉን ጉዳይ፤ ከባድ እያደረገው ነው፡፡ ብትመክሩት ይሻላል" ማለታቸውን ለፍኖተ-ነፃነት ዝግጅት ክፍል እንደገለጹ ጋዜጣው ዘግቦአል።

አቶ ዘሪሁን ለፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ በሰጡት መረጃ በምርመራ ሹሞቹ ሽምግልና ከተላኩት ቤተሰቦቻቸው አንዳንዶቹ በየዋህነት መርማሪው ፖሊስ ባለበት "ለምን የሚሉህን እሺ አትላቸውም? ይኸው መርማሪው ፖሊስ ምከሩት እያለን ነው፡፡ መፈታት አትፈልግም ወይ? ለእኛስ ለምን አታስብልንም?" በማለት ለመምከር እንደሞከሩና እዚያው መርማሪው ፖሊስ ፊት" ምኑን ነው እሺ የምለው?" በማለት ንዴታቸውን መቆጣጠር እስኪያቅታቸው እንደጮሁባቸው በዚህ የተደናገጡት ቤተሰብም "እኛ፤ ፖሊሱ ንገሩት ያለንን ነው እንዲሁ የነገርንህ፡፡ነገሩ ምን እንደሆነ የምናውቀው ሚስጥር የለም፡፡ ሁሉንም የምታውቀው አንተ ነህ" በማለት እንዳረጋጓቸውና ከዚያ በኋላ ነገሩን አንስተውባቸው እንደማያውቁ አስታውቀዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በአገራችን ውስጥ ያለውን የኑሮ ውድነት እያባባሰ ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በየጊዜው ገንዘብ እያተመ ወደ ገቢያ ውስጥ መልቀቁ እንደሆነ ባለሙያዎች አስታወቁ

ከጊዜ ወደጊዜ እጅግ እየተባባሰ ለመጣውና ለብዙ ሚሊዮን ዜጎቻችን የችጋር አረንቋ ውስጥ መውደቅ አይነተኛ ምክንያት የሆነው የኑሮ ውድነት መንስኤው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ገንዘብ አለአግባብ እያተመ ገቢያ ውስጥ በመልቀቁ እንደሆነ የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው የባንክ ባለሙያ ገለጹ።

በብሄራዊ ባንክ ከፍተኛ አማካሪና ኤክስፐርት የሆኑት እኚህ ባለሙያ እንደገለጹት፤ መላውን የአገሪቱን ህብረተሰብ እያንሳቀለ ያለው ኑሮ ውድነት ምንጩ ፤ የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ዘርፍ አስመዝግቤያለሁ በማለት የምዕራቡን አለም ሲያጭበረብርበት የኖረው የውሸት ጭንብል ድህረ ምርጫ 97 በተከሰተው አፈናና ግድያ ምክንያት በመገፈፉ ያለምንም ቅድመ ዝግጅት ልማታዊ መንግሥት መስሎ ለመታየት በተለያዩ ቦታዎች የጀመረውን የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ወጪ ለመሸፈን ሲባል የአገሪቱ ኢኮኖሚ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ብዛት ያለው ገንዘብ እየታተመ በመረጨቱ ነው።

አምባገነኑ መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ በተደጋጋሚ እንደሚናገሩት በተቀረው አለም ተከስቷል ከሚሉት የምግብ ምርቶች መቀነስና የነዳጅ ዋጋ ንረት ጋር እምብዛም ግንኙነት የሌለው የአገራችን የኑሮ ውድነት፤ በአገዛዙ አፍሴላዊ እስታቲክስ መሠረት ላለፉት 6 እና 7 አመታት በተከታታይ በታየው እድገት ምርታማነታችን ጨምሯል እየተባለም እንኳ የምግብና ሸቀጣሸቀጦች ዋጋ ከህዝባችን የመግዛት አቅም በላይ እየሆነ መሄዱ በየጊዜው እየታተመ የሚለቀቀው ገንዘብ የመግዛት አቅም እያጣ መምጣቱን ለመደበቅ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶአል ተብሎአል።

በህግና በሥርዓት በሚተዳደሩ አገሮች እንዲህ አይነቱን ልቅ የገንዘብ ሕትመት በመቆጣጠር የኑሮ ውድነት የህዝባቸውን ህይወት እንዳያመሰቃቅልና ማህበራውና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን እንዳያስከትል የሚከላከሉት የየአገሮቹ ብሄራዊ ባንኮች ሲሆኑ፤ መለስ ዜናዊ ታማኝነታቸውን እየለካ እንደፈለገ የሚሾማቸውና የሚሽራቸው የአገራችን ብሄራዊ ባንክ ባለሥልጣናት ግን ሃላፊነታቸውን በትክክል ለመወጣት ነጻነቱ የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ በየጊዜው ተጨማሪ ገንዘብ ለማሳተም ከመለስ ዜናዊ በስልክ የሚሰጣቸውን ቀጭን ትዕዛዝ ለማስቆም ቀርቶ ለአገርና ለህዝብ እንደማይጠቅም እንኳ ለማስረዳት አይችሉም እንደ ባለሙያው አስተያየት።

የአገራችንን የፍትህ ተቋማት በመቆጣጠር የፖለቲካ ባላንጣዎቹን በሽብርተኝነት ስም እየፈረጀ ለአመታት ወሂኒ እያወረዳቸው ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ ከአካላዊ እስር ቤት ውጪ ያለውን ሰፊ ህዝብ በኑሮ ውድነቱ በመቅጣት ሞራሉ በችጋር እንዲላሽቅ በዚህም የተነሳ ሁሉም ነፍሱን ለማቆየት በሚደረግ የዕለት ተዕለት ሩጫ ተጠምዶ ከፖለቲካ ውጪ እንዲሆን አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የተረዱ ጥቂቶች አይደሉም ።

የግንቦት 7 ንቅናቄ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በሥልጣን ላይ እስከቆየ ድረስ የህዝባችን መከራና ስቃይ ፍጻሜ እንደማይኖረው በተከታታይ እየገለጸ ነው።

## በጋምቤላ የወያኔ ደህንነት ሃላፊ የነበረውን አስገድለዋል የተባሉ መያዛቸው ተዘገበ

በጋምቤላ ክልል በቅርቡ ተካሂዶ የነበረው ግምገማ በቀሰቀሰው ችግር ምክንያት ለአገዛዙ ባለው ታማኝነት የደህንነት ሃላፊ ሆኖ በስውር ሲሰራ የነበረው ጌታቸው አንኮሬ የተባለው ሆድ አደር ያስገደሉት በግምገማው ደስተኛ ያልሆኑ የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት መሆናቸውን ኢሳት ከአካባቢው አገኙሁት ያለውን መረጃ ጠቅሶ ዘገበ።

እንደ ኢሳት መረጃ ጌታቸው አንኮሬ የህወሀት ሰላይ በመሆን የክልሉ ነዋሪዎችን ሲያሰቃይና እርስ በርሳቸው እንዲከፋፈሉ ሲያደርግ የኖረ ከመሆኑም በተጨማሪ የተለያዩ የግንኙነት መስመሮችን በመዘርጋት በአካባቢው ተወላጆች ላይ ከፍተኛ የሆነ የደህንነት ስጋት ሲፈጥር ቆይቶአል።

ጌታቸው አንኮሬ የተገደለው ከክልሉ ፕሬዚዳንት መኖሪያ ግቢ ስብሰባ ጨርሶ ወደ ቤቱ ከሄደ ቦኋላ ግቢው ውስጥ በበርካታ ጥይቶች ተደብድቦ ነው። ጥቃቱን የፈጸመው ከስራ የተቀነሰ ነባር የፖሊስ አባል ሲሆን፤ የአካባቢው ባለስልጣናት ዩኒፎርም አልብሰው አስርገው በማስገባት ሶስት ባለስልጣኖችን እንዲገድል ትእዛዝ ሰጥተውት እንደነበር ለማወቅ ተችሎአል ብሎአል ኢሳት።

እንደ ኢሳት መረጃ እንዲገደሉ የተባሉት ሁለት ሌሎች የወያኔ ሹሞች እንማን እንደሆኑ ያልታወቀ ሲሆን በአካባቢው በብዛት የሰፈሩት የፌደራል ፖሊስ አባላት ግድያውን ፈጽሟል የተባለውን ፖሊስና አንድ የወረዳ ባለስልጣን በቁጥጥር ስር ማዋላቸው ታውቋል።

በአካባቢው አሁንም ከፍተኛ ውጥረት ያለ ሲሆን፣ የፌደራል ፖሊስ አባላት መንገድ ላይ ያገኙነት ሁሉ እያስቆሙ ይፈትሻሉ። የክልሉ ተወላጆችና ወያኔ የሾማቸው የአካባቢው ባለስልጣናት ዜጎች ተወልደው ካደጉበት ቀየ ያለፍላጎታቸው በሰፈራ ስም እንዲፈናቀሉ መደረጉን እንደሚቃወሙት ኢሳት መረጃ ደርሶኛል ብሎአል።

ለአምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ታማኝ በመሆን ነዋሪዎችን ያለፍላጎታቸው እንዲፈናቀሉ በሚያደርጉ የአካባቢው ባለስልጣናት ላይ ነዋሪዎች እርምጃ መውሰድ መጀመራቸው ያስደነገጣቸው የክልሉ ባለስልጣናት ፣ ልዩ ጥበቃ እየተደረገላቸው መሆኑ ታውቆአል።

በጋምቤላ የሚፈጸመው የህዝብ መፈናቀል ከፍተኛ ተቃውሞ እየቀረበበት መሆኑ ይታወቃል። መለስ ዜናዊ ባለፈው ረቡ ዕ ለፓርላማ ተብዬው ሸንጎ ሪፖርት ሲያቀርብ በጋምቤላ የሚካሄደውን የሰፈራ ፕሮግራም የሚቃወሙት ከመንግስት ጋር የርእዮት አለም ልዩነት ያላቸው ሰዎች ናቸው በማለት የተለመደውን ቅጥፈት አስምቶአል።

በአገራችን ሰፊ የተፈጥሮ ደን የነበረው የጋምቤላ ክልል ከህንድና ከአረብ አገሮች ለመጡ ባለሃብቶች ነጻ ሊባል በሚችል ገንዘብ እየተቸበቸበ በመመንጠር ላይ እንደሆነ ሲታወቅ በጋምቤላ ልማት ከጀመሩ ባለሃብቶች 90 በመቶ የሚሆኑት የህወሃት አባላት እንደሆኑ የኦክላንድ ኢንስቲቲዩት ሪፖርት አጋልጦአል።

## የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ት/ቤቶች ከማስተማሪያነት ይልቅ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በየማሰልጠኛው ያሉ ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ከፆታዊ ጥቃት ስለመከላከል ትማራላችሁ ተብለው ይጠሩና ለወያኔ አባልነት እንዲመዘገቡ በግልጽ ይነገራቸውል ተብሎአል።

የግንቦት 7 ዘጋቢ በአብዛኛዎቹ የቴክኒኪና ሙያ ማሰልጠኛዎች ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው ተማሪዎችና ወላጆቻቸው እንዳረጋገጡት ትምህርት ቤቶቹ ከሙያ ማስተማሪያነት ይልቅ ወደ ወያኔ መመልመያ ጣቢያነት መቀየራቸውን ለማወቅ ተችሎአል። የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የነገይቷ ኢትዮጵያ ተስፋ የሆኑት የዛሬዎቹ ወጣቶች በወያኔ ስውር ተንኮል ሞራላቸው እንዲላሽቅ፤ በራስ የመተማመን ስሜት እንዳያዳብሩ፤ ፈሪዎችና ድንጉጦች እንዲሆኑ ሆን ብሎ እያደረገ መሆኑ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሊቆጨው ይገባል የሚለው ንቅናቄያችን ግንቦት 7 መላው ህዝባችን በተለይም ወጣቱ ትውልድ ከወያኔ አፈና ነፃ የሆነች አገር እንድትኖረን ለሚደረገው ትግል ሁሉም በያለበት ሆኖ የሚችለውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ ሲያስተላለፍ ቆይቶአል።

## በሽብርተኝነት የፈጠራ ክስ ረጅም እስር ከተፈረደባችው

. . . (ከገፅ 3 የዞረ)

በድለላና ሽምግልና የፈለገውን የሃሰት ምስክርነት ማግኘት ያልቻለው የወያኔ ምርመራ ክፍል ከዚያ በኋላ ወደ ጉልበት በማምራት፤ ለሁለት ወር ጨለማ ክፍል አስገብተው ለብቻቸው እንዳሰሩዋቸው፤ ሁለት ቀን ሙሉ እጅና እግራቸውን በማሰር ሰቅለው ሲቀጠቅጡዋቸው እንዳደሩና ድብደባው ያስከተለዉን ቁስል ለመታከም ህክምና እንደተነፈጉ በዚህም የተነሳ እስከ ዛሬ በሰውነታቸው ላይ የሚታይ ጠባሳ እንዳለ ይህንንም በደል ፍርድ ቤት ለተባለው አካል ገልጸው ምንም ሰሚ እንዳላገኙም ገልጸዋል።

ይህ ሁሉ ስቃይና መከራ የተፈራረቀባቸው የነጻነትና የፍትህ ታጋይ አቶ ዘሪሁን የወያኔ መርማሪዎች ቀደም ብለው ከዛቱባቸው የ20 አመት እስራት ሶስት አመት ብቻ ዝቅ ብሎ የአስራ ሰባት አመት ጽኑ እስራት ተፈርዶባቸዋል።

ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ በተመሣሳይ ሁኔታ በሌሎች ተከሳሾች ላይ በሃሰት መስክራ ነጻ እንድትለቀቅ በሃሰን ሺፋና በወያኔ አቃቤ ህግ የቀረበላትን መደለያ ልትቀበል ፍቃደኛ ባለመሆኗ የ14 ዓመት ጽኑ እስራትና የ35 ሺህ ብር ቅጣት እንደተላለፈባት ይታወቃል።

የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ አቶ ዘሪሁን የፃፉትን ሙሉ ደብዳቤ በቀጣይ ዕትሙ እንደሚያወጣው አስታውቆአል።


### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org